# ታዬ በአሜሪካ

ርሀብ ብቻ መስሎን
ሰውን የሚያዋርድ ሩህን የሚያስት ክብርን የሚነካ
ሥልጣንም ጠኔ ነው ታዬ በአሜሪካ።

ዘመናት አልቅሰን ተዘርግቶ እጃችን
ቅንጅትን ሰጥቶን ሊታበስ እንባችን።
እስላም ክርስቲያን ሳይለይ ብሔር ጎሳ
ከአድማስ እስከ አድማስ ሕዝቡ ሲነሳሳ።
ኃይሉን አስተባብሮ የተነሳ ጠላት
ታየ በአሜሪካ ጠብቆት በንቃት።
የበጎቹን በረት አጥሩን አጥብቁ
ተኩላው ተሰማርቷል እንዳትነጠቁ።

ርሀብ ብቻ መስሎን
ሰውን የሚያዋርድ ሩህን የሚያስት ክብርን የሚነካ
ሥልጣንም ጠኔ ነው ታዬ በአሜሪካ።

አትበል ፖለቲካ ከእንግዲህ በቃኝ
የአምላክ ቁጣ ነው ኃይሉን የነሳኝ።
በተሰጠህ ጸጋ አስብ በአእምሮህ
ከቃሉ እንዳትወጣ እንዳያስቱህ።
ሰላምና ፍቅር በቅንጅት መንፈስ
መጽሐፎች ያዙሀል እንድትመላለስ
እስላም ክርስቲያኑ ተነሳ ለፍትህ
የድሀዎች እንባ ደርሷል ለአምላክህ።

ርሀብ ብቻ መስሎን
ሰውን የሚያዋርድ ሩህን የሚያስት ክብርን የሚነካ
ሥልጣንም ጠኔ ነው ታዬ በአሜሪካ።

ሲታሰር ሲፈታ ለእኛ የመሰልን
ዛሬ ተገላልጾ ራቁቱን ታዬን
አመጣለሁ ሲለን ነፃነት ፍትህ
ታዬ ተደራጅቶ ድሉን ሊቀማህ።
እዩት ሲንፈራገጥ ተጠቅሞ ኃይሉን
አምባ ገነን ሆኖ ሊፈናጠጠን።
ጎብጧል ትክሻችን አይችልም ሸክም
ሕዝብ ያልወከለው እኛን አይመራም።

ርሀብ ብቻ መስሎን
ሰውን የሚያዋርድ ሩህን የሚያስት ክብርን የሚነካ
ሥልጣንም ጠኔ ነው ታዬ በአሜሪካ።

እንደ አልማዝ የሚያበራው ሞገስ ሲገፋፍ
ታዬ ምርጫው ሆኖ ክብሩን ሲያሳልፍ።
ተገላልጦ ታዬ በማፍያ ተከቦ
በአንድ ሻለቃ ጦር ኃይሉ ተንበርክኮ።
አድማሴን አስፍቼ እስቲ ልጠይቅህ
ለዕውቀት ዶክተሩ እድሜ ለበዛብህ።
የሽማግሌ ወግ ክብሩ የሸበት
ዋሽቶ ማስታረቅ ነው ወይንስ ማፋጀት።
የፈሰሰው እንባ የሰማዕታት ደም
በምድር በሰማይም መፋረዱ አይቀርም።
ርሀብ ብቻ መስሎን
ሰውን የሚያዋርድ ሩህን የሚያስት ክብርን የሚነካ
ሥልጣንም ጠኔ ነው ታዬ በአሜሪካ።
የተሰረቀ አልማዝ አይሆንም ሞገስ
ታዬ ምርጫው ሆኖ እንዲህ ሲንኳሰስ።
ምርጫው ስንሻው ስንጠብቀው ኖረን
ኃይሉን መከታ አድርጎ በግላጭ ዘረፈን።
አንድነት ይለናል እየጫረ እሳት
ትንሳኤን እንዳናይ ትግሉን ለማጥፋት።
በገዛ ብራችን ተጠቅመው አየርን
ስውር መልክተኞች የሚከፋፍሉን
የሻለቃ ምርጫው አሳፋሪ ጉድ
በታሪክ ይጻፋል ለመጪው ትውልድ።
ርሀብ ብቻ መስሎን
ሰውን የሚያዋርድ ሩህን የሚያስት ክብርን የሚነካ
ሥልጣንም ጠኔ ነው ታዬ በአሜሪካ።

ደብተራው ድህረ ገጽ ኢትዮ ላይን
ታጋይ በማዋረድ ለመጥቀም ማንን።
የኢሕአፓ አዛውንቶች እረ ምን ነካችሁ
በሰልሳ አምስት ሰባ እንዲህ መቅለላችሁ።
እንደ ሻማ ቀልጠው  በመሩን መንገድ
በሰማዕታት ደም ይቅር መነገድ።
ወንድምና እህቴ እናትና አባቴ
ለነፃነት ፍትህ ያሉ ዱሩ ቤቴ።
ውድ የኢሕአፓ ልጆች የተሰውለት
ለአንድ ኢትዮጵያ ነው ለሕዝብ ቅንጅት።
ርሀብ ብቻ መስሎን
ሰውን የሚያዋርድ ሩህን የሚያስት ክብርን የሚነካ
ሥልጣንም ጠኔ ነው ታዬ በአሜሪካ።

በዲያስፖራው አለም ከእስክሪኑ ጀርባ
በኢዛና መሪነት ምትፈጽሙ ደባ።
ሕዝቡን ለመበተን ሌት ከቀን ምትጥሩ

ጊዜያችሁ አሁን ነው ዛሬ ተመከሩ።
ትልቁን ባላንጣ ወያኔን አስቀምጠን
እርስ በእርስ መፋጀት ምንድነው ሚጠቅመን።
እኔ ነኝ የማቅልህ ሚባልበት ዘመን
ተሰናብቶ ሄዷል ዳግም ላይመጣብን።
ኢሕአፓም ቅንጅት ድርጅቶች ሁሉ
ሚያዝያ ሰላሳን ቆም ብላችሁ አስተውሉ።
ጠንቅቆ ያውቀዋል ሕዝቡ ሚያዋጣዉን
ወሬውን ትታችሁ አሳዩን ተግባሩን።

**ርሀብ ብቻ መስሎን**
**ሰውን የሚያዋርድ ሩህን የሚያስት ክብርን የሚነካ**
**ሥልጣንም ጠኔ ነው ታዬ በአሜሪካ።**

( 27.09.2007 ተፃፈ ከ የአጽብአሔ በርን-- ስዊዘርላንድ )

{ቅንጅት የሁለት አመት ወይንም ግለሰቦች እንደፈቀዱ የሚያደርጉት ደካማ ድርጅት ነው የምትሉ የዋሆች ካላችሁ ይህንን ልንነግራችሁ አበክረን እንፈልጋለን።

- ቅንጅት በኢትዮጵያ ምድር በፍትህ እና ነፃነት ጥያቄ ዙርያ በተለያዩ ድርጅቶቸ ተሰባሰበው ውድ ሕይወታቸውን የከፈሉ የዕልፍ አዕላፋት የደም ውጤት ነው።

- በአንድ ሌሊት ሦስታና አራት ልጆቻቸውን በፋሽስቶች አሳርደው አዕምሮአቸውን በመሳት የትም ወድቀዉ የቀሩ የብዙ ኢትዮጵያውያን እናቶች የልጆቻቸው የደም ውጤት ነው።

- ልጆቻቸውን በትነው በፋሽስቶች ጥይት ተደብድበው በየወንዙ ዳር ተጥለው ጅቦች የገነጣጠሏቸው የብዙ ኢትዮጵያውያን አባቶች የደም ውጤት ነው።

- አፍላ የወጣትነት ዘመናቸውን ለኢትዮጵያ ፍትህ ነፃነት ሲታገሉ በፋሽስቶች ታፍነው
የተደበደቡ፣ በዘይት የተጠበሱ፣ በሻማ የተለበለቡ፣ ሰውነታቸው የተተለተለ የዚያ ትውልድ ፈርጦች የደም ውጤት ነው።

- ከዚያ ሁሉ ሰቆቃ ለመትረፍ በአራቱም ማዕዘን እንደ ጎርፍ የኢትዮጵያን ጋራ ሸንተረር በጠፍ ጨረቃ በእግር በማቋረጥ ድንበሮችን ተሻግረው ዛሬ በአለም ዙሪያ ተበትነው በስደት፣ በውርደት ሕይወታቸውን የሚገፉ የብዙ ኢትዮጵያውያኖች የመጨረሻ ተስፋቸው ነው። “ የመጪውም ትውልድ ተስፋ ነው።“

- እነዚህ ኢትዮጵያኖች በሀገራቸው ምድር እፎይ ብለው በነፃነት መኖርን ይሻሉ። ለሀገራቸውም የችሎታቸውን ለማድረግ ተዘጋጅተዋል። ይህም ሊሆን ተስፋ የሚደረገው በዘር፣ በሃይማኖት፣ ብብሔርና  በጎሳ ያልተለያየው በዘመናት እንባና ደማችን ከአምላክ የአገኘነው ሁሉም በአንድነት የተሰባሰበበት ቅንጅት ነው። ይህንን ድርጅት ለመጠበቅ በንቃት እንደምንገኝ ሚያዝያ 30/ 1997 ዓ.ም. በታየው ነፃነትና ፍትህ በጠማው የሕዝብ ጎርፍ ቃል እንገባላችኋለን። }